# አንድ ቀን ...

አንድ ቀን እያልኩኝ አንዱ ቀን አለፈ
ሌላ ቀን ስጠብቅ እሱም ቶሎ ላፈ።
ዛሬው ነገ ሆኖ ነገው ተነገ ወዲያ
ቅጽበት ወደ ሰአት ሰአቱ ወደ ወራት የለውም ማለቂያ።
ያ አንዱ ቀን እኔ የምጠብቀው
መጠበቅ ብቻ እንጂ ላንገናኝ ነው።
ወይስ ይሆን እንዴ አበሻን መቅጠር
ይዘገያል እንጂ ይመጣል ላይቀር።
ወይስ ይሆን እንዴ ጭራሽ ቀጠሮ አልባ
በይመጣል አይቀር አንጀት የሚያባባ።
ስንት አስርት ቆጠርኩኝ ስንቱስ ቀን አለፈ
አሁንስ ተገደድኩ ለማለት ከነፈ።
ያበሻ ቀጠሮ አይቀርም እያልኩ
ስንት አመት መባቻን ሳሰላ ከረምኩ።
ይመሻል ይነጋል ቀኑ ይቆጠራል
አንድ ቀን ስጠብቅ የኔ ዕድሜም ይከንፋል።
ባህታን ስዘክር ደሞ ሥላሴን
አቦ ብቅ ሲሉ ደርሰው ዕለቱን
ደግሜ ዳግሜ ሳከብር ልደታን
ዛሬስ ከቁም ቆጠርኩ መጠባበቄን።
ጎርጊስ ነው እያልኩኝ ምን ያመጣ ስል
ስብከቱን ሳልጨርስ ገብርኤልም ከች ሲል።
ቀኑ ቀንን ወልዶ ወራቱ አመታት
ያቺ ቀን ላትመጣ ላይቀርም ዕልፈት።
ያቺ ቀን ትመጣ ስጠብቅ ሰባጅ
ዛሬስ መጠበቂያ ስፍራ አጣሁኝ እንጅ።

**ክንፈ ሚካዔል**

**ነሀሴ 27፣ 2000 ዓ/ም**